# የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ

## አጠቃላይ ትምህርት

### የለዉጥ ሀሳቦች

ነሐሴ 14- ቀን 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አቅራቢ ፣ አክሊሉ ዳለሎ

# በጥናቱ የተሳተፉ ምሁራን

| ቅድመ-መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ | ሁለተኛ ደረጃ | የመምህራን ዝግጅትና ልማት |
|---|---|---|
| ፕ/ሮ ጥሩሰዉ ተፈራ | ፕ/ሮ አማረ አስገዶም | ፕ/ሮ አክሊሉ ዳለሎ |
| ዶ/ር አብዱላዚዝ ሁሴን | ዶ/ር አምቢሳ ከነዓ | ዶ/ር አብረሃ አስፋዉ |
| ዶ/ር ባለዉ ደምሴ | ዶ/ር ዳዊት አስራት | ፕ/ሮ ዳርጌ ወሌ |
| ዶ/ር በላይ ሀጎስ | ዶ/ር ደረጀ አንዳርጌ | ዶ/ር ዳዊት መኮንን |
| ዶ/ር ደሜ አበራ | ፕ/ሮ ተስፋዬ ስመላ | ፕ/ሮ ድርብሳ ዱፌራ |
| ዶ/ር ግርማ ለማ | ዶ/ር የቆየዓለም ደሴ | ዶ/ር ፈቀደ ቱሉ |

# የሚቀርቡ ዋና ዋና ነጥቦች
# (የለዉጥ ሃሳቦች)

## ክፍል አንድ፡ ሥርአተ-ትምህርት፤ ሥነዘዴና ምዘና

ሀ. ሥርአተ-ትምህርት

ለ. የመማር-ማስተማር አካባቢና ሥነዘዴ

ሐ. ምዘናና ፈተና

መ. ተያያዥ ጉዳዮች

## ክፍል ሁለት፡ የመምህራን ሥልጠናና ልማት

ሀ. የእጩ መምህራን ምልመላ

ለ. የእጩ መምህራን ሥልጠና

ሐ. ምደባና ዝውውር

መ. ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ

ሠ. ጥቅማጥቅሞችና የማትጊያ ዘዴዎች

ረ. የልቀት ማዕከላት ማቋቋም

ሰ. ሁሉ-አቀፍ የመምህራን ፖሊሲ ማዘጋጀት

ሸ. የመምህርነትን ሙያ ገጽታ መገንባት

# ክፍል አንድ፡ ሥርአተ-ትምህርት፤ ሥነዘዴና ምዘና

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት

- **የትምህርትን መሰረት** ለማጠንከር 0-ክፍል በአዲስ መልክ ይደራጃል፤
  - 0-ክፍል የ4-5+ ዕድሜ የላቸዉን ህጻናት ይይዛል
  - ሥርዓተ ትምህርቱ የህጻናትን **ሁለንተናዊ ዕድገት** (አካላዊ፤ አእምሮአዊ፤ ማህበራዊ፤ ስሜታዊ) በሚያመጣ መልኩ ይቀረጻል
    - **ከአካባቢ ጋር** እንዲቆራኝም ይደረጋል

# ክፍል አንድ፡...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት **መሠረታዊ ክህሎቶችን** (ማንበብ፤ ማስላት፡ አካባቢን ማወቅና መጠበቅ፤ ወዘተ) የማዳበር ዓላማዉን የበለጠ እንዲያጠናክር ይደረጋል፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎችን ለከፍተኛ ደረጃ ከማዘጋጀቱም በተጨማሪ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ያበቃል
  - ስለሆነም የሙያ ትምህርት (vocational education) **በሁሉም ደረጃዎች ይካተታል**

# ክፍል አንድ፡...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- ከቅድመ-መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለዉ ሥርአተ ትምህርት ብቃትን (competence) መሠረት ያደረገና የሙያ ጽንሰ-ሃሳቦችንና ክህሎቶችን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ፣
  - የሥርአተ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ፣ ከአካዳሚያዊ እና ከሙያ ክህሎት ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ፣
    - መሠረታዊ ክህሎት፣ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ ክህሎትን በማካተት ማስተማር፣

# ክፍል አንድ፡...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የቋንቋ፣ የሒሳብና የሣይንስ ትምህርቶችን ጥራት ማሳደግ፣
- ቴክኖሎጂ ነክ ጽንሰ-ሃሳቦችና ክህሎቶች ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በጥንቃቄ ማካተታቸዉን ማረጋገጥ፣
  - ቴክኖሎጂ የሚፈጥረዉንም ዕድል ለትምህርት ጥራት ማሳሳያ መጠቀም (e-learning)

# ክፍል አንድ፡...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- ሥርዓተ ትምህርቱ አገራዊ አግባብነት ያለውና በአለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚችልእንዲሆን ማድረግ፣
- ሥነጥበብ በሁሉም ደረጃዎች ትኩረት እንዲያገኝ ይደረጋል
- ሥርዓተ ትምህርቱ በተቻለ መጠን የየአካባቢዉን ፍላጐት መሠረት ያደረገ ና ተለማጭ እንዲሆን ማድረግ፣

# ክፍል አንድ፣...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- ሥርዓተ ትምህርቱ ተማሪዎች ብዙሃነትን የሚያከብር አንድነት እንዲያጐለብቱ የሚያግዝ እንዲሆን ማድረግ፣
  - የታሪክ፣ የጂአግራፊ፣ የተግባቦት፣ ወዘተ. ትምህርቶችን ለዚህ ዓላማ መጠቀም፣
  - በዋናነት ሁሉም መምህር የሥነዜጋና ሥነምግባር መምህር እንዲሆን ማብቃት

# ክፍል አንድ፡...

## ለ. የመማር-ማስተማር አካባቢና ሥነዘዴ

- አሃዳዊ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደገና እንዲታይ
  - ዘዴዉ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት አሁን ባለንበት ሁኔታ የሚሠራ አይደለም
- በሕፃናት መካከል ያሉትን ልዩነቶች (ልዩ ተሰጥኦ፣ ክህሎት፣ ወዘተ. ) የሚያስተናግድ የመማር ሁኔታ መፍጠርና የማስተማር ዘዴን መጠቀም፣
- የትምህርት ሥነዘዴን ከመማር ዉጤት ጋር (learning outcomes) ማቆራኘት

# ክፍል አንድ፣...

## ለ. የመማር-ማስተማር አካባቢና ሥነዘዴ...

- ትምህርት ከክፍል በተጨማሪ በመስክ እና በተግባር እንዲካሄድ ማድረግ
  - አሳታፊና ችግር ፈቺነትን የሚያበረታታ ማድረግ
- በቅድመ መደበኛ ደረጃ ጨዋታ ዋንኛዉ ዘዴ አድርጎ መጠቀም፣
  - ህጻናትን ያማከለ፤ እናቅስቃሴ የሚያደፋፍር

# ክፍል አንድ፣...

## ሐ. ምዘናና ፈተና

- ተማሪዎች አስፈላጊውን የመማር ውጤት *(minimum learning competencies)* አምጥተው ትምህርታቸውን ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ፣
  - ምዘና እውቀትን ብቻ ሳይሆን ክህሎትን፣ አመለካከትን፣ እምቅ አቅምን እንዲመዘን ማድረግ፣
    - ለዚህም ስክት ከወረቀት ፈተናዎች በተጨማሪ የምልከታ ክህሎትን፤ ነገሮችን ተንትኖ የማቅረብ ብቃትን፤ በኘሮጀክትና በጽሑፍ ሥራዎች አማካይነት መመዘን፣
- የክፍል ምዘና ተከታታይ እንዲሆን ማድረግ፣

# ክፍል አንድ፡...

## ሐ. ምዘናና ፈተና...

- ክልላዊና አገር አቀፍ ፈተናዎች የብቃት ምዘና *(competence test)* ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣
  - ክልላዊ ፈተና 6ኛ ክፍል መጨረሳ
  - አገር አቀፍ ፈተናዎች 8ኛ እና 12ኛ ክፍሎች መጨረሳ
- አገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለችበትን ሁኔታ ለመገምገም የአለም አቀፍ ምዘና አባል በመሆን መሳተፍ፣

# ክፍል አንድ፡...

## መ. ተያያዥ ጉዳዮች

- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃና የመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የለጳና ግዴታ ትምህርት (0-G8)እንዲሆን ማድረግ፣
  - የገቢ አቅማቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ለሚመጡ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የድጋፍ ሥርአት መፍጠር (ምሳሌ፡ ምግብና የመማሪያ ቁሳቁስ)፣

# ክፍል አንድ፡...

## መ. ተያያዥ ጉዳዮች...

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የዝቅተኛውን መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ መሸከም በሚችል መልኩ ማስፋፋት፣
- ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የአካዳሚክና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች ተለይተዉ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በፌዴራል እና በክልሎች ራሱን በቻለ አደረጃጀት ተዋቅሮ እንዲሰራ ማድረግ፣

# ክፍል ሁለት፡ የመምህራን ሥልጠናና ልማት

## ሀ. የእጩ መምህራንን ምልመላ

- በዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምደባ ወቅት የመምህርነትን ሙያ እንደ አንድ የሥልጠና መስክ (BAND) እንዲካተት ማድረግ፣
- የመምህራን አሠልጣኞችን ለመለየት፣ ለማዘጋጀትና ለማልማት የሚያስችል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁሉም ተቋማትና እጩዎች ገዢ የሆነ የመመልመያ መስፈርት ማዘጋጀት
  - የኮታ አሠራርን ማስወገድ/በኮታ ለሚመጡ የተለየ ድጋፍ መስጠት፣

# ክፍል ሁለት፡...

## ሀ. የእጩ መምህራንን ምልመላ...

- እጩ መምህራንን 12ኛ ክፍልን የተሻለ ውጤት ካመጡት ውስጥ መምረጥ፣
  - ለሙያዉ ፍላጎትና አክብሮት እንዳላቸዉም ማረጋገጥ
- አሠልጣኝ ተቋማት በምልመላ ወቅት ቀጥተኛና ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤

# ክፍል ሁለት፡...

## ለ. የእጩ መምህራንን ሥልጠና

- በሁሉም ደረጃዎች የእጩ መምህራንን ሥልጠና ጥራት ማሻሻል
  - የመምህራን ትምህርት ሥርአተ ትምህርት እጩ መምህራን ከምረቃ በኋላ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣
  - የመምህራን ሥልጠናና የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዲጣጣም ማድረግ፣

# ክፍል ሁለት፡...

## ለ. የእጩ መምህራንን ሥልጠና...

- ብቁና በቂ መምህራንን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ **የተለያዩ አማራጮችን** መጠቀም፡
  - የተጣመረውን (concurrent)፣
  - ከመጀመሪያ ድግሪ ቀጥሎ የሚሰጥ የሙያ ሥልጠና (consecutive)፣ እና
  - ሌሎችንም

# ክፍል ሁለት፡...

## ለ1. የሥልጠና አካባቢና ሥነዘዴ፡

- ለመስክና ተግባር ተኮር ዘዴ የተለየ ትኩረት መስጠት
- መሠረታዊ ክህሎት፣ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ከፍተኛ የአስተሳሰብ ክህሎትን በተመጣጠነ መልኩ ማስተማር፣
- የቅድመ መደበኛ መማህራንን ዝግጅት በተለየ መልኩ ማከናወን (ለምሳሌ፤ ለጨዋታ ልዩ ትኩረት መስጠት)

# ክፍል ሁለት፡...

## ለ2. መሠረታዊ የሥልጠና ደረጃዎች፣

- ለቅድመ-መደበኛና ለመጀመሪያ ደረጃ በ12+3 ደረጃ የሰለጠኑ፣
- ለዝቅተኛ ሁለተኛ ደረጃ (7-10)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣
- ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ (11-12) ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው፣

# ክፍል ሁለት፡...

## ሐ. ምደባና ዝውውር

- በሁሉም ደረጃ የመምህራን ምደባ ግልጽና ፍትሓዊ እንዲሆን ማድርግ
- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝውውርን በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት እንዲሠራ ማድረግ፣
  - ብዙሃነትን በሚያጐለብት መልኩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምደባ ማካሄድ፣
- የትኩረት ነጥብ፡
  - መምህራን በአንድ ቦታ ረዘም ያለ ጊዜ መቆየት ብዙ ጥቅም ስላለዉ የዝዉዉር ጥያቄ እንዳያስቡ የሚያደርጉ ስልቶች የተገበራሉ፤

# ክፍል ሁለት፡...

## መ. ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ

- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራምን በትምህርት ቤትም ሆነ በኮሌጆች ተቋማዊ ማድረግ፣
  - ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም በመምህራን ፍላጎት የሚወሰን ሆኖ የትምህርት አይነት እውቀትና የማስተማር ዘዴ ዝግጁነት ክፍተቶችን እንዲሞላ ተድርጐ እንደገና ማሻሻል፣
  - የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም ከደረጃ እድገት ጋር እና ከሙያ ፍቃድና እድሳት ጋር ማስተሳሰር፣
    - ለዚህም የሚሆን የመምህራን የብቃት ማዕቀፍ (Teachers' Qualification Framework) ይዘጋጃል፤

# ክፍል ሁለት፡...

መ. ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ....

- የክረምት የትምህርት ዋንኛ ዓላማ ደረጃ ማሳደግ ሳይሆን ሙያ ማሻሻል እንዲሆን ማድረግ፣
  - እንደአማራጭ የማታ ትምህርት፤ ሙሉ ስኮላርሺፕ፤ ወዘተ መጠቀም
- ደረጃ ያሻሻሉ መምህራን በዚያዉ ደረጃ ጥቅማጥቅማቸዉ ተጠብቆ የሚቆዩበት ሥርዓት መዘርጋት

# ክፍል ሁለት፡...

## ረ. ጥቅማጥቅሞችና የማትጊያ ዘዴዎች፣

- የመምህራን ደመወዝ ቢያንስ ቢያንስ ከሌሎች ሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ/ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ፣
- ጥቅማጥቅሞችን ማለትም ቤት፣ ትራንስፖርት፣ ነፃ ሕክምና፣ በጡረታ ወቅት ሙሉ ደመወዝ፣ በዝቅተኛ ወይም ያለ ወለድ የብድር አገልግሎት፣ ወዘተ. ማቅረብ፤
  - በአስቸጋሪ ቦታና ሁኔታ ለሚሰሩ መምህራን አበላቸውን እንዲሁም ሌሎች ፓኬጆችን በተጠና መንገድ ማሻሻል፣
    - መብራት በሌለበት ሶላር ፓኔሎችን መስጠት፤
    - ትንስ መሬት (ለጎመን የሚሆን)
- አሁን ያሉ ጥሩ ጅምሮች ተጠናክረዉ ይቀጥሉ፡
  - የመኖሪያ ቤት አቅርቦት
  - የመምህራን ሆስፒታል

# ክፍል ሁለት፡...

## ረ. ጥቅማጥቅሞችና የማትጊያ ዘዴዎች፤...

- ማራኪና መምህራንን በጥረታቸዉና ችሎታዉ ልክ ለይቶ የሚክስ እርከን ማዘጋጀት
  - ጭማሪዎች ጊዜያቸዉን ጠብቀዉ መፈጸማቸዉን ማረጋገጥ
- የነጻ ትምህርት ዕድል (በማታም፣ በቀንም)
- ከፍተኛ ችሎታ፤ ልምድ፤ ፍላጎትና ዝንባሌ የላቸዉን መምህራን በማወዳደረ ርዕሰ መምህር የሚሆኑበትን ሥርዓት መዘርጋት

# ክፍል ሁለት፡...

## ሰ. የልቀት ማዕከላት ማቋቋም

- በየክልሉ ቢያንሰ አንድ፣ የቅድመ-መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ የመምህራን ትምህርት የልሕቀት ማእከል ማደራጀት፣
- በሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት ላይ የሚሠሩ በሚገባ የተደራጁ የልህቀት ማእከላት ማደራጀት፤
- በመምህራን ትምህርት ላይ ትኩረት አድርገዉ የሚሰሩ የትምህርት ዩኒቨርስቲዎች ማቋቋም፣
- አንድ አገር አቀፍ የመምህራ ትምህርት ምርምር እና የስትራቴጂ ኢንስቲትዩት መመሥረት፣

# ክፍል ሁለት፡...

## ሸ . ሁሉ-አቀፍ የመምህራን ፖሊሲ ማዘጋጀት

- የመምህራንና የመምህራን አሠልጣኞችን፡
  - ምልመላ፣
  - መረጣ፣
  - የሥራ ላይ ሥልጠና፣
  - እውቅና የመስጠት፣
  - ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ፣
  - የሙያ ፍቃድ፣
  - ዝውውር፣
  - አገልግሎትን የማቋረጥ ፣ ወዘተ. ያካተተ መሆን ይጠበቅበታል፣
- የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ማካተት፤

# ክፍል ሁለት፡...

## ቀ. የመምህርነትን ሙያ ገጽታ መገንባት

- አሁን ያለዉ የተዛባ እይታ በመሠረቱ አንዲቀየር ማድረግ። እንዴት?
  - እስካሁን የተዘረዘሩ የለዉጥ ሀሳቦች ተግባር ላይ በማዋል
  - የሙያዎችን ምንነትና ጠቀሜታ ለተማሪ ዎላጆች ማስገንዘብ
  - የመንግሥት ሃላፊዎችና ተዋቂ ሰዎች ስለመምህርነት ሙያ ጠቀሜታ ተከታታይነት ያለዉ ምሥክርነት እንዲሰጡ ማድረግ
  - የላቀ አስተዋጽዖ ያበረከቱ መምህራንን በከፍተኛ ደረጃ ዕውቅና መስጠት
  - በትምህርት ቤቶች ክበባት መመሥርት (ምሳሌ፤ የነጌዉ መምህር)
  - ወዘተ...

# አመሰግናለሁ!!!